# ማስታወሻ

**ከ፡ ብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር)**

**ለ፡ ብልፅግና ፓርቲ ምክር ቤት አባላት**

**ቀን፡ 21/12/2017 ዓ.ም**

**ጉዳዩ፡- አንዱ ዓመት እንደ አምስት**

ቀጣዩ 2018 የኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ “ከተስፋ ወደሚጨበጥ ብርሃን” የሚሸጋገርበት ዓመት ነው፡፡ በርግጥ ይህ ዕቅዳችን እንደተሳካ የሚያሳዩ ምልክቶችን በዚህ ዓመት ተመልክተናል፡፡ በቱሪዝም፣ በዲጂታል ዘርፍ፣ በግብርና፣ በማዕድንና በአምራች ዘርፍ ያየናቸው ለውጦች እና ዕድገቶች ካሰብነው ቀድመን “ወደሚጨበጥ ብርሃን” መድረሳችንን አረጋግጠዋል፡፡ የኢትዮጵያ የዘመናት ስብራቶች ተጠግነው ኢትዮጵያ ማንሠራራት ጀምራለች፡፡ ይሄው የሕዳሴ ግድባችንም ተጠናቅቆ፣ የዘመናትን የትውልድ ጥያቄ መልሶ፣ የሚጨበጥ ብርሃን እየሆነ ነው፡፡

በዚህ የተነሣ መጪ 2018 ዓመት ለኢትዮጵያ ወሳኝ ዓመት ነው፡፡ መጪው ዓመት ያቀድነውን ሳይሆን ካቀድነው አምስት እጥፍ በላይ የምናከናውንበት ዓመት ነው፡፡ በለውጡ ዘመን አንዱን ዓመት ብዙ ማድረግ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ እያመረትን ዓመቱን በግብርና ሦስት እና አራት አድርገነዋል፡፡ ሌትና ቀን፣ በሳምንት ሰባት ቀናት በመሥራት የዓመታት ፕሮጀክቶች በወራትና በቀናት እየተጠናቀቁ ናቸው፡፡ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በቅደም ተከተል ሳይሆን በተመሳሳይ ጊዜ በማከናወን የዓመታትን ሥራ ወደ ወራት እያመጣነው ነው፡፡ በዚህም የተነሣ አንድ ዓመት ሁለትና ሦስት ሆኖ መቆጠሩ እየተለመደ ነው፡፡

ይሄንን አዲስ የሥራ ባህል የበለጠ ተላብሰን፣ ቀጣዩ 2018 ዓመት የአምስት ዓመታት ሥራ የምናከናውንበት ዘመን ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ ሰዓት - የአምስት ሰዓት፣ በእያንዳንዱ ቀን - የአምስት ቀን፣ በእያንዳንዱ ሳምንት - የአምስት ሳምንት፣ በእያንዳንዱም ወር - የአምስት ወር ሥራ መከናወኑን ማረጋገጥ አለብን፡፡ በ2018 አንድ ቀን አንድ ብቻ አይደለም፡፡ አምስት ነው፡፡ የአንድ ቀን መባከንም እንደ አምስት ቀናት መባከን የሚቆጠር ነው፡፡ ግምገማችንም በዚሁ መንገድ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በ2018

አንዱን ዓመት እንደ አምስት ዓመት በመሥራት በዋናነት የሚከተሉትን ማከናወን ይኖርብናል፡፡

- **ሰላምን የበለጠ ማጽናት፡-** በጸናው የፓርቲያችንና የመንግሥታችን አቋም፣ የፓርቲያችን ምክር ቤትም በቅርቡ በወሰነው መሠረት፣ ቀጣዩ ዓመት ለሰላም የበለጠ የምንሠራበት ዓመት ይሆናል፡፡ የትጥቅ ዐመጽ የሚያዋጣ መስሏቸው ጫካ የገቡትን አካላት በሁሉም ዓይነት የሰላም አማራጮች ወደ ሰላማዊ መድረክ ማምጣት አለብን፡፡ በከተማና በገጠር ሆነው በእገታ፣ በአሻጥር፣ በውንብድና፣ በተደራጀ ወንጀልና በኮንትሮባንድ የተሠማሩትን በላቀ የጸጥታና የፖለቲካ ሥራ ተከታትለን ለሕግ ማቅረብ ይኖርብናል፡፡ የሸቀጦች እና የሰዎች ዝውውር ያለ ምንም እንከን እንዲከናወን የአካባቢያችንን ጸጥታ ራሳችን ማስከበር አለብን፡፡

  የ2018 የሰላም ሁኔታችን የሚለካው በእገታ፣ በአሻጥር፣ በውንብድና፣ በተደራጀ ወንጀልና በኮንትሮባንድ መቀነስ፣ ወደ ሰላም በተቀላቀሉ ታጣቂዎች ብዛትና ዓይነት፣ በሸቀጦችና በሰዎች ሰላማዊ ዝውውር እንከን አልባነት ነው፡፡

- **መልካም አስተዳደር፡-** በውሳኔያችን መሠረት የሕዝባችንን ብሶት የሚያባብሱ፣ የመንግሥትን አገልግሎት በዝምድና እና በገንዘብ የሚሸጡ፣ የመንግሥትን የሥራ ሰዓት ለግል ጥቅም የሚያውሉ፣ ኃላፊነታቸውን በብቃት የማይወጡ፣ በአጠቃላይ የብልጽግና ጉዟችንን በየተቋማቱ የሚያደናቅፉ አካላትን በማረምና ወደ ሥርዓት በማስገባት፣ መልካም አስተዳደር በየተቋማቱ እንዲሰፍን ማድረግ አለብን፡፡

  የ2018 የመልካም አስተዳደር ስኬታችን የሚለካው በየተቋማቱ ሕዝባችን ባገኘው የአገልግሎት ርካታ ልክ ነው፡፡

- **ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ፡-** አመራሩና አባላቱ በየቦታው የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በጥራትና በጊዜ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ ሀብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ፕሮጀክቶችን ለማደናቀፍና ለማጓተት ምክንያት የሚሆኑትን ሁሉ ማስተካከል፣ ማረምና መቅጣት ያስፈልጋል፡፡

  የ2018 የፕሮጀክት አፈጻጸም ስኬታችን የሚለካው በየአካባቢው ከጊዜያቸው ቀድመው በጥራት በተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ልክ ነው፡፡

- **የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ሥምረት፡-** በቀጣዩ ዓመት በሁሉም ዘርፍ የሚካሄዱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ሆነው ከታቀደላቸው በላይ እንዲከናወኑ አመራሩና አባላቱ በቅርበት፣ በንቃትና በትኩረት መከታተል አለባቸው፡፡

በግብርና፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም፣ በገቢ ማሰባሰብ፣ በአምራችነት፣ በሸቀጦች ንግድ፣ በዲጂታይዜሽን፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ወዘተ. የሚከናወኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ያለ እንከን በቅልጥፍናና የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያችንን ግብ በሚያሳካ መንገድ እንዲከናወኑ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

እነዚህ ዘርፎች በ2018 ተሳኩ የምንለው ከታቀደላቸው በአምስት እጥፍ ከተሳኩ ብቻ ነው፡፡

- **ምርጫ፡-** 2018 ሰባተኛው ሀገራዊ ምርጫ የሚከናወንበት ዓመት ነው፡፡ ይህ ምርጫ ፍትሐዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ተአማኒ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ማድረግ ዋና ተልዕኳችን ነው፡፡ ምርጫው ካለፉት ምርጫዎች በሁሉም መመዘኛዎች የተሻለ፣ ለቀጣይ ዴሞክራሲያዊ ጉዞ መስፈንጠሪያ በሚሆን መንገድ መከናወን አለበት፡፡ ለዚህም አመራርና አባላት ለምርጫው እንደ አንድ ተወዳዳሪ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፍኖት መሣለጥ ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ ሚናቸውን በላቀ ሁኔታ መወጣት አለባቸው፡፡

  የ2018 ምርጫ ስኬት የሚለካው ካለፉት ዓመታት በፍትሐዊነቱ፣ በዴሞክራሲያዊነቱና በተአማኒነቱ እጅግ የተሻለ በመሆኑ ነው፡፡

በ2018 እነዚህን ተግባራት ለማከናወን፣ ከአመራርና ከአባላት ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ፡፡ የመጀመሪያው 2018 አንድ ዓመት ብቻ አለመሆኑን ዐውቆ ዝግጅትንም ሆነ ሥራን በአምስት ዓመት መለካት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የአምስት ዓመታትን ሥራ በአንድ ዓመት ለማከናወን የሚያስችል ቆራጥነትና የሥራ ትጋት ነው፡፡

የፓርቲያችን አመራርና አባላት፣ የ2018ን የዕቅድ አፈጻጸምን በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በየመንፈቅ ዓመቱና በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ ስንገመግም፣ በአምስት ዓመት ልኬት እንደምንገመግም ቀድማችሁ በመረዳት፣ አስፈላጊውን ሁሉ ዝግጅት እንድታደርጉ ከወዲሁ አሳስባለሁ፡፡